በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ.ቁ 216709

ቀን፡- 1/4/2014 ዓ.ም

**ዳኞች** ፡- ሱልጣን አባተማም

ምፅላል ኃይለ

ዋዚሞ ዋሲራ

**አመልካች**፡ቾች- እነ ኦሜጋ የወርቅ ግብይት ማህበር ጠበቃ አክሊሉ ኤርሚያስ

**ተጠሪ**፡/ዎች- እነ አቦቦ ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤት

መዝገቡ ከቀነ ቀጠሮ በፊት ሊቀርብ የቻለው አመልካች 30/3/2014 ዓ.ም በተፃፈ ቃለ መሃላ አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ለዚህ ችሎት 16/3/2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የጋምቤላ ብ/ክ/መ/ጠ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01080/2014 በ 16/3 /2014 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፆ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ በዚህ መሰረት መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ትአዛዝ ሰጥተናል፡፡

# ትዕዛዝ

ያሁኑ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ይሁን የምንሰራውን ፈቃዳችን ነጥቆ እንዳንሰራ አደረገን የሚል ሲሆን ፍ/ቤት ግራቀኝ በፍሬ ነገር ሣያከራክር የመክሰስ መብት የላችሁም በማለት የወሰነበት አግባብነት

መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብለናል፡፡

1.መጥሪያ ለተጠሪ/ዎች/ ይድረስ ብለናል፡፡ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክራቸውን በሬጅስትራር ፅ/ቤት በኩል ይቀባበሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቀጠሮ ለ 25/4/2014 ዓ.ም ተቀጥሮአል፡፡ 5፡20 ሰዓት

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*